# “ባቢሎን በቋንቋ ፈረሰች”

ታሪኩ አባዳማ የካቲት 2001

ስለ ባቢሎናውያን ድሮ ከነብስ አባታችን የሰማሁት ታሪክ የሀተታዬ መንደርደሪያ እንዲሆን የመረጥኩት አለምክንያት አይደለም። ስለ ባቢሎን ኢምፓየር ትምህርት ቤት በታሪክ ክፍለ ግዜ የተማርኩት እና የነብስ አባታችን የነገሩን ነገር የሚለያይ ቢሆንም ፤ የአባታችን ስብከት ከአገራችን ማህበራዊ ዕውነት ጋር ሲነፃፀር መልዕክቱ ቀላል ግምት የማይሰጠው ሆኖ አግኝቸዋለሁ። አገራችን የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት እንደመሆኗ ከአባታችን ስብከት የምትቀስመው ቁምነገር አለ።

እንደ አባታችን አገላለፅ የባቢሎን ሰዎች በዘመኑ ጥበብ እና ስልጣኔ እጅግ የላቀ ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር። ታዲያ ይህ ስልጣኔ በሰጣቸው ፀጋ ተኩራርተው እግዚአብሔርን እስከ መናቅ እና እንዲያውም ከሰማይ አድነው ከክብሩ ሊያወርዱት ያስመኛቸዋል። ያሰቡትን ለመፈፀም ወደ ሰማይ የሚያደርሳቸው ፎቅ መገንባት ይጀምራሉ። ግምባታው ወደ ላይ ከፍ ባለ መጠን ፈጣሪ ካለበት የተጠጉ መስሏቸው እሱን ለመውጋት የሰላ ጦር ሽቅብ ያምዘገዝጉ ጀመር። ይህን ያስተዋለው ፈጣሪ የጦሩን ጫፍ ቀይ እየቀባ ይመልስላቸዋል። ባቢሎናውያን በሞራል ‘ይኸው አገኘነው’ እያሉ ወደ ፈጣሪ ጦር መስበቃቸውን ቀጠሉ። ይሁንና ባድራጎታቸው እጅግ ያዘነው ፈጣሪ የመግባቢያ ቋንቋቸውን ሰወረባቸው። እርስ በርስ መግባባት ተሳናቸው ፣ አንዱ የሚለውን ሌላው ሊገባው አልቻለም። በመካከላቸው አለመደማመጥ ፣ አለመግባባት እና ንትርክ እየተባባሰ ሄዶ በመጨረሻ ችግሩ ጠንዝቶ አቅማቸው በመዳከሙ በጠላቶቻቸው እጅ ወደቁ። ግምባታ ቆመ ፣ ባቢሎን በመግባቢያ ቋንቋ እጦት ፈረሰች።

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከነደፆር (605 - 508 ከክርስቶስ ልደት በፊት) እየሩሳሌምን ወርሮ ወደ ትቢያ መቀየሩ ፣ የሰለሞንን ቤተ-መቅደስ ማቃጠሉ እንደ ታላቅ ጥፋት የሚነገር ታሪክ ቢሆንም በዚያ ዘመን ወደር የማይገኝለት ስልጣኔ እና ወታደራዊ ሀይል ገንብቶ እንደነበር ይታወቃል። እንደ ታሪክ ፀሀፊዎች ከሆነ የባቢሎን ኢምፓየር የጠፋው ከሱ ላቅ ባለ አቋም በተነሳው የፐርሺያ ጦር ነው። እግዜር ቀብቶ ልኮልኛል የሚል ሲረስ የተባለ የፐርሺያ ንጉስ ባቢሎንን አምበርክኮ የጠፋውን የኢየሩሳሌም መዲና እንደገና በመገንባት የተቃጠለውን ቤተ-መቅደስም አንፁዋል።

የጹሁፌ አላማ የባቢሎንን ታሪክ በዝርዝር ለማተት ባለመሆኑ ወደ ነብስ አባታችን ሰበካ ልመልሳችሁ። የሳቸው ሰበካ ዋና ትኩረት እግዜርን የተጋፋ መጨረሻው አያምርም የሚል መልዕክት ያዘለ ነው። ምንም ያህል ብትደረጁ ከሀያሉ አምላክ ልቆ መታየት አይቻልም የሚል መልዕክት አለው። ልጆች ለነበርነው ደግሞ ጥጋባችሁን በልክ አድርጉት ማለታቸው ጭምር ነበር። ለዛሬው ሀተታ ይጠቅማል ብዬ የወሰድኩት ግን (የጥጋብ ነገር እንደ ተጠበቀ ሆኖ) የባቢሎን ብርቱ ክንድ በመግባቢያ ቋንቋ እጦት መዛሉን እና ለመጥፊያ ምክንያትም ይኸው መሆኑን ከሚያመለክተው ነጥብ ላይ ነው።

የራስን ሀሳብ ለሌሎች ለመግለፅ ፣ የሌሎችንም ሰምቶ ለመረዳት መግባቢያ ቋንቋ ፣ ድልድይ የግድ ያስፈልጋል። እኛ የመግባቢያ ቋንቋ ችግር የለብንም። ይኸው በአማርኛ እየተነጋገርንም አይደል። የኛ ችግር አባ ከገለፁት የባቢሎናውያን ችግር ትንሽ ለየት ይላል። የኛ ችግር በምንነጋገርበት አንድ ቋንቋ መግባባት ፣ መደማመጥ አለመቻላችን ነው። ከባቢሎናውያን ጋር የምንመሳሰለው ደግሞ የችግራችን አቢይ ምንጭ ሀሳብ መለዋወጥ ፣ መደማመጥ የተሳነን ከመሆኑ ላይ ነው። ባቢሎናውያን ቋንቋ ተደበላልቆባቸው ሀሳባቸውን መለዋወጥ ፣ መደማመጥ አልቻሉም ፤ እኛ ሀሳብ ተደባላልቆብን ባንድ ቋንቋ መግባባት ፣ መደማመጥ አልቻልንም። ባቢሎናውያን የቋንቋ ድልድይ ተሰብሮባቸው ተሰባብረዋል - እኛ የቋንቋን ድልድይ መጠቀም ተስኖን እየተንገዳገድን ነን።

እንግሊዛዊው የታሪክ ተመራማሪ ኤጄፒ ቴይለር እንደሚለው “ከታሪክ የምንማረው ብቸኛ ነገር ቢኖር ከታሪክ የምንማራቸው ነገሮች አለመኖራቸው ነው”። “The only lesson of history is that there are no lessons of history”. ከታሪክ መማር ብንችል ኖሮ አባ የሰበኩን የባቢሎን ታሪክ ምንኛ በጠቀመን ነበር።